# የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ፡፡

Ethiopians' Citizen Democratic Union | Union Citoyenne Démocratique des Éthiopiens

www.slttunhzb.net sh1@ttomar.net


ገ_ዐዓ_20140101_ዐማርኛ

የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ የ2014 ፡ ዓ.ም. ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ መልእክት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፦

## የሙት ፡ ይዘት ፡ ትድገት ፥ የለም ፡ በዐዲስ ፡ ዓመት !

ለንደን ፥ መስከረም ፡ 1 ፡ ቀን ፥ 2014 ፡ ዓ.ም. ።

**የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ!**

ላለፉት ፡ ሠላሳ ፡ ዓመታት ፦

- ላልሠራኽው ፡ "ሕገ፡መንግሥት" ፣ ለሕገ ፡ ውንብድና ፡ ካልተገዛኽ ፡ እያለ ፡ ሲጨቀጉኽ ፥
- የኢትዮጵያ ፡ አንድያ ፡ ባለቤትነትኽን ፡ በመካድ ፡ "ሕዝቦች" ፡ እያለ ፡ እየመነዘረኽ ፡ ሀገርኽ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ባለቤት ፡ አልባ ፡ ሲያደርግብኽ ፥
- እንደ ፡ እንስሳ ፡ በ"ክልል" ፡ ሲያግድኽ ፥
- ከታሪካውያን ፡ ጠላቶችኽ ፡ ጋራ ፡ ለጥፋትኽ ፡ ሲዶልትብኽና ፡ ባለቤት ፡ አልባ ፡ ሀገርኽን ፡ ሲቄራርስብኽና ፡ ሲያስበዘብዝብኽ ፡

የኖረውን ፡ ከሓዲውንና ፡ ንኁለተኛውን ፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፥ እንሆ ፥ በአንድነት ፡ ክንድኽ ፡ ዐናቱን ፡ ወያኔ-ሕ.ወ.ሓ.ት.ን ፡ ቀልተኽ ፡ ብታሸቀነጥርበትም ፥ ቅሬታ ፡ አካሉ ፡ "ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ.-ብልጽግና፡ፓርቲ-ሸኔ" ፡ ባፈሰሰለት ፡ የመሰንበቻ ፡ ዐቅም ፡ አንሰራርቶ ፥ አረመኔያዊ ፡ የፈሪ ፡ በትሩን ፡ ዳግም ፡ ሲያሳርፍብኽ ፡ ከርሟል ። አንተም ፡ ልትመክተውና ፡ ፈጽመኽ ፡ ልትደመስሰው ፡ ቄርጠኽ ፡ በመነሣት ፥ የተቀላ ፡ ራሱ ፡ ወደወደቀበት ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንሆ ፡ ተመኻል ።

"የዐዞ ፡ ክፋቱ ፥ ፊት ፥ ጥርሱ ፤ ኋላ ፥ ጅራቱ ።"

ነውና ፥ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ተቄርጦ ፡ እና ፡ አድብቶ ፡ የቄየ ፡ ቅሬታ ፡ አካሉን ፡ ፈጥነኽ ፡ ካላስወገድከውና ፡ መላ ፡ ሀገርኽ ፡ ኢትዮጵያን ፡ መልሰኽ ፡ እጅኽ ፡ ካላገባኻት ፡ በቀር ፥ አኹንም ፡ ከዠርባኽ ፡ ተከድተኽ ፡ መሥዋዕትኽ ፡ ኹሉ ፡ አላንዳች ፡ ጥርጥር ፡ ከንቱ ፡ ይኾንብኻል ።

ዐዲሱ ፡ ዓመት ፡ 2014 ፡ ዓ.ም. ፥ የፍጹም ፡ ድል ፡ ዓመት ፡ እንዲኾንልኽ ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ ውጥን ፡ አካልኽ ፡ የኾነው ፡ **የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት** ፡ (ኢ.ሀ.ሥ.አ.) ፡ ከልብ ፡ ይመኝልኻል ።

www.slttunhzb.net sh1@ttomar.net

ጥንተ ፡ ጠላትኽን ፡ ፋሺስት ፡ ኢጣልያን ፡ ሚያዝያ ፡ 27 ፡ ቀን ፡ 1933 ፡ ዓ.ም. ፡ በዐርበኞችኽ ፡ ተጋድሎ ፡ ድል ፡ ብታደርጋትም ፥ ፍጹም ፡ ድል ፡ የተገኘው ፡ ግን ፥ ከመንፈቅ ፡ በኋላ ፥ ኅዳር ፡ 18 ፡ ቀን ፡ 1934 ፡ ዓ.ም. ፥ እጥንተ ፡ መዲናኽ ፡ ጐንደር ፡ ላይ ፡ መሽጎ ፡ የነበረው ፡ ቅሬታ ፡ አካሏ ፡ በዐርበኞችኽ ፡ ክንድ ፡ የተደመሰሰ ፡ ዕለት ፡ ነበር ። ዛሬም ፥ በሰማንያኛ ፡ ዓመቱ ፥ ባዲሱ ፡ ዓመት ፡ መባቻ ፥ ፈጽመኽ ፡ በምትተማመንበት ፡ አምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኀይል ፡ ጸንተኽና ፥ ሀገራዊ ፡ ሰራዊትኽን ፡ በጠራ ፡ አመራር ፡ እፊትኽ ፡ አሰሰልፈኽ ፦

1) ወያኔ–ሕ.ወ.ሐ.ት.ን ፡ ፈጽመኽ ፡ የምትደመስስበትና ፥ አለቆቹን ፡ ለፍርድ ፡ የምታቀርብበት ፥

2) የወያኔ–ሕ.ወ.ሐ.ት. ፡ ቅሬታ ፡ አካል ፡ የኾነውን ፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ቅሬታ ፡ ይዘት ፡ ገርስሰኽ ፡ በመጣል ፥ ከዛሬዋ ፡ መዲናኽ ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ፈጽመኽ ፡ የምታስወግድበት ፥

3) መላ ፡ ሀገርኽን ፡ ተቈጣጥረኽ ፥ ዳር ፡ ድንበሯን ፡ የምታስከብርበት ፥

4) በግፍ ፡ የታሰሩ ፡ ልጆችኽን ፡ የምታስፈታበትና ፡ የምትክስበት ፥

5) ሀገር ፡ ኢትዮጵያን ፡ የከዱና ፡ ያስበዘበዙ ፣ በደም ፡ የታጠቡ ፡ መንደር ፡ ገነኖችንና ፡ ሆድኛ ፡ ዐዳሪዎች ፡ ግብር ፡ ዐበሮቻቸውን ፡ ለፍርድ ፡ የምታቀርብበት ፥

6) ሀገራዊ ፡ እግዚእናኽን ፡ በማስከበር ፥ ሥልጡንሕዝባዊት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ባዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ (ባዲስ ፡ ክዋኔ) ፡ ዳግም ፡ የምትከውንበት ፥

7) አንድነትን ፣ ነጻነትን ፣ ፍትሕን ፣ ሰላምንና ፡ ልማትን ፡ የምታገኝበት ፡

ዓመት ፡ እንዲኾንልኽ ፡ **የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ፡ (ኢ.ሀ.ሥ.አ.)** ፡ ከልብ ፡ ይመኝልኻል ፤ በምትፈጽመው ፡ ተጋድሎኽም ፡ ኹሉ ፡ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ከጐንኽ ፡ አይለይም ❖

ትሑት ፡ አገልጋይኽ ፦

**ኢ.ሀ.ሥ.አ.**